# ትንቢተ ፡ ዳንኤል ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፣ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ከበባት ።

2 ፤ ጌታም ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ከፍሎ ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ ርሱም ፡ ወደሰናዖር ፡ ምድር ፡ ወደአምላኩ ፡ ቤት ፡ ወሰደው ፣ ዕቃውንም ፡ ወደአምላኩ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አገባው ።

3 ፤ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውንና ፡ መልከ ፡ መልካሞቹን ፣ በጥበብ ፡ ኹሉ ፡ የሚያስተውሉትን ፡ ዕውቀትም ፡ የሞላባቸውን ፡ ብልኀተኛዎችና ፡ አስተዋዮች ፡ የኾኑትን ፣ በንጉሡም ፡ ቤት ፡ መቆም ፡ የሚችሉትን ፡ ብላቴናዎች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከነገሥታቱና ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ዘር ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፣ የከለዳውያንንም ፡ ትምህርትና ፡ ቋንቋ ፡ ያስተምሯቸው ፡ ዘንድ ፣ ለጃን ፡ ደረባዎች ፡ አለቃ ፡ ለአስፋኔዝ ፡ ነገረ ።

5 ፤ ንጉሡም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያሳድጓቸው ፡ ዘንድ ፣ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፣ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከሚጠጣውም ፡ ጠጅ ፡ በየዕለቱ ፡ ድርጓቸውን ፡ አዘዘላቸው ።

6 ፤ በእነዚህም ፡ መካከል ፡ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዳንኤልና ፡ ዐናንያ[262] ፡ ሚሳኤልና[263] ፡ ዐዛርያ[264] ፡ ነበሩ ።

7 ፤ የጃን ፡ ደረባዎቹም ፡ አለቃ ፡ ስም ፡ አወጣላቸው ፤ ዳንኤልን ፡ ብልጣሶር[265] ፣ ዐናንያንም ፡ ሲድራቅ[266] ፣ ሚሳኤልንም ፡ ሚሳቅ ፣ ዐዛርያንም ፡ ዐብደናጎ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

8 ፤ ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ መብልና ፡ በሚጠጣው ፡ ጠጅ ፡ እንዳይረክስ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ፤ እንዳይረክስም ፡ የጃን ፡ ደረባዎቹን ፡ አለቃ ፡ ለመነ ።

9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጃን ፡ ደረባዎቹ ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ለዳንኤል ፡ ሞገስንና ፡ ምሕረትን ፡ ሰጠው ።

10 ፤ የጃን ፡ ደረባዎቹም ፡ አለቃ ፡ ዳንኤልን ፦ መብሉንና ፡ መጠጡን ፡ ያዘዘላችኹን ፡ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ እፈራለኹ ፤ በዕድሜ ፡ እንደናንተ ፡ ካሉ ፡ ብላቴናዎች ፡ ይልቅ ፡ ፊታችኹ ፡ ከስቶ ፡ ያየ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፣ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በራሴ ፡ ታስፈርዱብኛላችኹ ፡ አለው ።

11 ፤ ዳንኤልም ፡ የጃንደርባዎቹ ፡ አለቃ ፡ በዳንኤልና ፡ በዐናንያ ፡ በሚሳኤልና ፡ በዐዛርያ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ ሜልዳርን ።

12 ፤ እኛን ፡ ባሪያዎችኽን ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ትፈትነን ፡ ዘንድ ፣ እለምንኻለኹ ፤ የምንበላውንም ፡ ጥራጥሬ ፡ የምንጠጣውንም ፡ ውሃ ፡ ይስጡን ፤

13 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእኛን ፡ ፊትና ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ የሚበሉትን ፡ የብላቴናዎችን ፡ ፊት ፡ ተመልከት ፤ እንዳየኸውም ፡ ኹሉ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ የወደድኸውን ፡ አድርግ ፡ አለው ።

14 ፤ ይህንም ፡ ነገራቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ፈተናቸው ።

15 ፤ ከዐሥር ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከበሉ ፡ ብላቴናዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ፊታቸው ፡ አምሮ ፡ ሥጋቸውም ፡ ወፍሮ ፡ ታየ ።

---

262ዕብ. ፣ ሐናንያህ ፡ (ምሕረተ ፡ እግዚአብሔር) ።
263ዕብ. ፣ ሚሻኤል ፡ (ማን ፡ እግዚአብሔር) ።
264ዕብ. ፣ ዐዛርያ ፡ (እግዚአብሔር ፡ የሚረዳው) ።
265ዕብ. ፣ ብልጥሻጻር ።
266ዕብ. ፣ ሻድራክ ።



www.ethiopianorthodox.org

16 ፤ ሜልዳርም ፡ መብላቸውንና ፡ የሚጠጡትን ፡ ጠጅ ፡ አስቀርቶ ፡ ጥራጥሬውን ፡ ሰጣቸው ።

17 ፤ ለእነዚህም ፡ ለአራቱ ፡ ብላቴናዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ዅሉ ፡ ዕውቀትንና ፡ ማስተዋልን ፡
ሰጣቸው ፤ ዳንኤልም ፡ በራእይና ፡ በሕልም ፡ ዅሉ ፡ አስተዋይ ፡ ነበረ ።

18 ፤ እነርሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡ ፡ ያዘዘው ፡ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የጃን ፡ ደረባዎቹ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡
ናቡከደነጾር ፡ ዘንድ ፡ አገባቸው ።

19 ፤ ንጉሡም ፡ በተነጋገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከብላቴናዎቹ ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ዳንኤልና ፡ እንደ ፡ ዐናንያ ፡ እንደ ፡ ሚሳኤልና ፡
እንደ ፡ ዐዛርያ ፡ ያለ ፡ አልተገኘም ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

20 ፤ ንጉሡም ፡ በጠየቃቸው ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ በግዛቱ ፡ ዅሉ ፡ ከሚኖሩ ፡ የሕልም ፡
ተርጓሚዎችና ፡ አስማተኛዎች ፡ ዅሉ ፡ እነርሱ ፡ ዐሥር ፡ እጅ ፡ የበለጡ ፡ ኾነው ፡ አገኘባቸው ።

21 ፤ ዳንኤልም ፡ እስከንጉሡ ፡ እስከቂሮስ ፡ መዠመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በነገሠ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ናቡከደነጾር ፡ ሕልም ፡ ዐለመ ፤ መንፈሱም ፡ ታወከ ፥ እንቅልፉም ፡
ከርሱ ፡ ራቀ ።

2 ፤ ለንጉሡም ፡ ሕልሙን ፡ እንዲነግሩት ፡ ንጉሡ ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹንና ፡ አስማተኛዎቹን ፡ መተተኛዎቹንና ፡
ከለዳውያኑንም ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፥ አዘዘ ፤ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

3 ፤ ንጉሡም ፦ ሕልም ፡ ዐልሜያለኹ ፥ ሕልሙንም ፡ ለማወቅ ፡ መንፈሴ ፡ ታውኳል ፡ አላቸው ።

4 ፤ ከለዳውያኑም ፡ ንጉሡን ፡ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ ለባሪያዎችኽ ፡ ሕልምኽን ፡
ንገር ፥ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳይኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

5 ፤ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ከለዳውያኑንም ፦ ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ፤ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡
ባታስታውቁኝ ፥ ትቈረጣላችኹ ፡ ቤቶቻችኹም ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረጋሉ ።

6 ፤ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ ግን ፡ ብታሳዩ ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ስጦታና ፡ ዋጋ ፡ ብዙ ፡ ክብርም ፡ ትቀበላላችኹ ፤ ስለዚህም ፡
ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ አሳዩኝ ፡ አላቸው ።

7 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፡ መልሰው ፦ ንጉሡ ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ሕልሙን ፡ ይንገር ፥ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳያለን ፡ አሉት ።

8 ፤ ንጉሡ ፡ መልሶ ፦ ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ታውቃላችኹና ፡ ጊዜውን ፡ እንድታስረዝሙ ፡ እኔ ፡
ዐውቃለኹ ።

9 ፤ ሕልሙንም ፡ ባታስታውቁኝ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ አለባችኹ ፤ ጊዜውን ፡ ለማሳለፍ ፡ የሐሰትንና ፡ የተንኰልን ፡ ቃል ፡
ልትነግሩኝ ፡ አዘጋጅታች኿ል ፤ ስለዚህ ፥ ሕልሙን ፡ ንገሩኝ ፥ ፍቺውንም ፡ ማሳየት ፡ እንድትችሉ ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

10 ፤ ከለዳውያኑም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሰው ፦ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
የለም ፤ ከነገሥታትም ፡ ታላቅና ፡ ኀይለኛ ፡ የኾነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚንና ፡ አስማተኛን ፡
ከለዳዊንም ፡ አልጠየቀም ።

11 ፤ ንጉሡም ፡ የሚጠይቀው ፡ ነገር ፡ የቸገረ ፡ ነው ፤ መኖሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ካልኾነ ፡ ከአማልክት ፡ በቀር ፡
በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የሚያሳየው ፡ ማንም ፡ የለም ፡ አሉ ።

12 ፤ ስለዚህም ፡ ንጉሡ ፡ ተበሳጨ ፡ እጅግም ፡ ተቈጣ ፥ የባቢሎንንም ፡ ጠቢባን ፡ ዅሉ ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

13 ፤ ትእዛዝም ፡ ወጣ ፥ ጠቢባንንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ዠመሩ ፤ ዳንኤልንና ፡ ባልንጀራዎቹንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡
ፈለጓቸው ።

14 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ የወጣውን ፡ የንጉሡን ፡ የዘበኛዎቹ ፡ አለቃ ፡



www.ethiopianorthodox.org

አርዮክን ፡ በፈሊጥና ፡ በማስተዋል ፡ ተናገረው ፤

15 ፤ ለንጉሡም ፡ አለቃ ፡ ለአርዮክ ፡ መልሶ ፦ የንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቸኰለ ፧ አለው ። አርዮክም ፡ ነገሩን ፡ ለዳንኤል ፡ አስታወቀው ።

16 ፤ ዳንኤልም ፡ ገብቶ ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ የሚያስታውቅበት ፡ ጊዜ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡን ፡ ለመነ ።

17 ፤ 18 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ። ዳንኤልም ፡ ባልንጀራዎቹም ፡ ከቀሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ጠቢባን ፡ ጋራ ፡ እንዳይሞቱ ፡ ስለዚህ ፡ ምስጢር ፡ ምሕረትን ፡ ከሰማይ ፡ አምላክ ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፥ ነገሩን ፡ ለባልንጀራዎቹ ፡ ለዐናንያና ፡ ለሚሳኤል ፡ ለዐዛርያ ፡ አስታወቃቸው ።

19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ምስጢሩ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ ለዳንኤል ፡ ተገለጠለት ፤ ዳንኤልም ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ አመሰገነ ።

20 ፤ ዳንኤልም ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ጥበብና ፡ ኀይል ፡ ለርሱ ፡ ነውና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይባረክ ፤

21 ፤ ጊዜያትንና ፡ ዘመናትን ፡ ይለውጣል ፤ ነገሥታትን ፡ ያፈልሳል ፥ ነገሥታትንም ፡ ያስነሣል ፤ ጥበብን ፡ ለጠቢባን ፡ ዕውቀትንም ፡ ለአስተዋዮች ፡ ይሰጣል ።

22 ፤ የጠለቀውንና ፡ የተሰወረውን ፡ ይገልጣል ፤ በጨለማ ፡ ያለውን ፡ ያውቃል ፥ ብርሃንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

23 ፤ ጥበብንና ፡ ኀይልን ፡ የሰጠኸኝ ፥ እኛም ፡ የለመንኸን ፡ ነገር ፡ አኹን ፡ ያስታወቅኸኝ ፥ አንተ ፡ የአባቶቼ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ አስታውቀኸኛልና ፥ እገዛልኻለኹ ፡ አመሰግንኻለኹ ።

24 ፤ ከዚህም ፡ በዃላ ፡ ዳንኤል ፡ ንጉሡ ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወዳዘዘው ፥ ወደ ፡ አርዮክ ፡ ገባ ፤ በገባም ፡ ጊዜ ፦ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ አታጥፋ ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገባኝ ፥ እኔም ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ አሳያለኹ ፡ አለው ።

25 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አርዮክ ፡ ዳንኤልን ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገባውና ፦ ከይሁዳ ፡ ምርኮኛዎች ፡ ያለውን ፡ ለንጉሡ ፡ ፍቺውን ፡ የሚያስታውቀውን ፡ ሰው ፡ አግኝቻለኹ ፡ አለው ።

26 ፤ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ብልጣሶርም ፡ የሚባለውን ፡ ዳንኤልን ፦ ያየኹትን ፡ ሕልምና ፡ ፍቺውን ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፧ አለው ።

27 ፤ ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ንጉሡ ፡ የጠየቀውን ፡ ምስጢር ፡ ጠቢባንና ፡ አስማተኛዎች ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ ቃላተኛዎች ፡ ለንጉሡ ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ፤

28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምስጢር ፡ የሚገልጥ ፡ አምላክ ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፥ ርሱም ፡ በዃለኛው ፡ ዘመን ፡ የሚኾነውን ፡ ለንጉሡ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ አስታውቆታል ። በዐልጋኽ ፡ ላይ ፡ የኾነው ፡ ሕልምና ፡ የራስኽ ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ።

29 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በዃላ ፡ የሚኾነው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በዐልጋኽ ፡ ላይ ፡ ታስብ ፡ ነበር ፤ ምስጢርንም ፡ የሚገልጠው ፡ የሚኾነውን ፡ ነገር ፡ አስታውቆኻል ።

30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ምስጢር ፡ ለእኔ ፡ መገለጡ ፡ ፍቺው ፡ ለንጉሡ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፥ አንተም ፡ የልብኽን ፡ ዐሳብ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ በጥበብ ፡ ስለ ፡ በለጥኹ ፡ አይደለም ።

31 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ታላቅ ፡ ምስል ፡ አየኽ ፤ ይህም ፡ ምስል ፡ ታላቅና ፡ ብልጫልጫታው ፡ የበዛ ፡ ነበረ ፥ በፊትኽም ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ መልኩም ፡ ግሩም ፡ ነበረ ።

32 ፤ የዚህም ፡ ምስል ፡ ራስ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፥ ደረቱና ፡ ክንዶቹም ፡ ብር ፥ ሆዱና ፡ ወገቡም ፡ ናስ ፥

33 ፤ ጭኖቹም ፡ ብረት ፥ እግሮቹም ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ ነበረ ።

34 ፤ እጅም ፡ ሳይነካው ፡ ድንጋይ ፡ ከተራራው ፡ ተፈንቅሎ ፡ ከብረትና ፡ ከሸክላ ፡ የኾነውን ፡ የምስሉን ፡ እግሮች ፡ ሲመታና ፡ ሲፈጭ ፡ አየኽ ።

35 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብረቱና ፡ ሸክላው ፥ ናሱና ፡ ብሩ ፡ ወርቁም ፡ በአንድነት ፡ ተፈጨ ፥ በመከርም ፡ ጊዜ ፡ በዐውድማ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እብቅ ፡ ኾነ ፤ ነፋስም ፡ ወሰደው ፥ ቦታውም ፡ አልታወቀም ፤ ምስሉንም ፡ የመታ ፡ ድንጋይ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ኾነ ፡ ምድርንም ፡ ፈጽሞ ፡ ሞላ ፡

36 ፤ ሕልሙ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ ፍቺውን ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ እንናገራለን ።

37 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ መንግሥትንና ፡ ኀይልን ፥ ብርታትንና ፡ ክብርን ፡ የሰጠኽ ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

38 ፤ በሚቀመጡበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ የሰው ፡ ልጆችንና ፡ የምድር ፡ አራዊትን ፡ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶኻል ፥ ለኹሉም ፡ ገዢ ፡ አድርጎኻል ፤ አንተ ፡ የወርቁ ፡ ራስ ፡ ነኽ ።

39 ፤ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ከአንተ ፡ የሚያንስ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ይነሣል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ የናስ ፡ መንግሥት ፡ ይነሣል ።

40 ፤ አራተኛውም ፡ መንግሥት ፡ ኹሉን ፡ እንደሚቀጠቅጥና ፡ እንደሚያደቅ ፡ ብረት ፡ ይበረታል ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ እንደሚፈጭ ፡ ብረት ፡ ይቀጠቅጣል ፡ ይፈጭማል ።

41 ፤ እግሮቹና ፡ ጣቶቹም ፡ እኩሉ ፡ ሸክላ ፡ እኩሉም ፡ ብረት ፡ ኾኖ ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ የተከፋፈለ ፡ መንግሥት ፡ ይኾናል ፤ ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ እንዳየኹ ፥ የብረት ፡ ብርታት ፡ ለርሱ ፡ ይኾናል ።

42 ፤ የእግሮቹም ፡ ጣቶች ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፥ እንዲሁ ፡ መንግሥቱ ፡ እኩሉ ፡ ብርቱ ፡ እኩሉ ፡ ደካማ ፡ ይኾናል ።

43 ፤ ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ ከሰው ፡ ዘር ፡ ጋራ ፡ ይደባለቃሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብረት ፡ ከሸክላ ፡ ጋራ ፡ እንደማይጣበቅ ፥ እንዲሁ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አይጣበቁም ።

44 ፤ በእነዚያም ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይፈርስ ፡ መንግሥት ፡ ያስነሣል ፤ ለሌላ ፡ ሕዝብም ፡ የማይሰጥ ፡ መንግሥት ፡ ይኾናል ፤ እነዚያንም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ትፈጫቸዋለች ፡ ታጠፋቸውማለች ፥ ለዘለዓለምም ፡ ትቆማለች ።

45 ፤ ድንጋዩም ፡ እጅ ፡ ሳይነካው ፡ ከተራራ ፡ ተፈንቅሎ ፡ ብረቱንና ፡ ናሱን ፡ ሸክላውንና ፡ ብሩን ፡ ወርቁንም ፡ ሲፈጨው ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚኾነውን ፡ ታላቁ ፡ አምላክ ፡ ለንጉሡ ፡ አስታውቆታል ፤ ሕልሙም ፡ እውነተኛ ፡ ፍቺውም ፡ የታመነ ፡ ነው ።

46 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ለዳንኤል ፡ ሰገደለት ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ ያቀርቡለት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

47 ፤ ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፦ ይህን ፡ ምስጢር ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ተችሎኻልና ፥ በእውነት ፡ አምላካችኹ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፥ የነገሥታትም ፡ ጌታ ፥ ምስጢርም ፡ ገላጭ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

48 ፤ ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገው ፥ ብዙም ፡ ታላቅ ፡ ስጦታ ፡ ሰጠው ፥ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ፥ በባቢሎንም ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ አደረገው ።

49 ፤ ዳንኤልም ፡ ንጉሡን ፡ ለመነ ፥ ርሱም ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሾማቸው ፤ ዳንኤል ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በር ፡ ነበረ ።

__________________ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ የኾነውን ፡ የወርቁን ፡ ምስል ፡ አሠራ ፤ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ በዱራ ፡ ሜዳ ፡ አቆመው ።

2 ፤ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ መኳንንትንና ፡ ሹማምቶችን ፥ አዛዦችንና ፡ ዐዛውንቶችን ፥ በጅሮንዶችንና ፡ አማካሪዎችን ፥ መጋቢዎችንም ፥ አውራጃ ፡ ገዢዎችንም ፡ ኹሉ ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ላከ ።

3 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ መኳንንቱና ፡ ሹማምቶቹ ፥ አዛዦቹና ፡ ዐዛውንቶቹ ፥ በጅሮንዶቹና ፡ አማካሪዎቹ ፥ መጋቢዎቹና ፡


www.ethiopianorthodox.org

አውራጃ ፡ ገዢዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ናቡከደነጾርም ፡ ባቆመው ፡ ምስል ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

4 ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪውም ፡ እየጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የምትናገሩ ፡ ሆይ ፥

5 ፤ የመለከትንና ፡ የእንቢልታን ፥ የመሰንቆንና ፡ የክራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፥ ተደፍታችኹ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንድትሰግዱ ፡ ታዝችኋል ።

6 ፤ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ።

7 ፤ ስለዚህ ፥ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢልታውን ፥ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፥ የበገናውንና ፡ የዘፈኑንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የተናገሩ ፡ ኹሉ ፡ ተደፉ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቅ ፡ ምስል ፡ ሰገዱ ።

8 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከለዳውያን ፡ ቀርበው ፡ አይሁድን ፡ ከሰሱ ።

9 ፤ ለንጉሡም ፡ ለናቡከደነጾር ፡ ተናገሩ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ። ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

10 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፦ የመለከትንና ፡ የእንቢልታን ፥ የመሰንቆንና ፡ የክራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ተደፍቶ ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ ይስገድ ፤

11 ፤ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ፡ ብለኽ ፡ አዘዝኽ ።

12 ፤ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሾምኻቸው ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ የሚባሉ ፡ አይሁድ ፡ አሉ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝኽን ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ፤ አማልክትኽን ፡ አያመልኩም ፥ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አይሰግዱም ።

13 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በብስጭትና ፡ በቍጣ ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ እነዚህንም ፡ ሰዎች ፡ ወደንጉሡ ፡ ፊት ፡ አመጧቸው ።

14 ፤ ናቡከደነጾርም ፦ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ ሆይ ፥ አምላኬን ፡ አለማምለካችኹ ፥ ላቆምኹትም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አለመስገዳችኹ ፡ እውነት ፡ ነውን ፧

15 ፤ አኹንም ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢልታውን ፡ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፡ የበገናውንና ፡ የዋሽንቱን ፡ የዘፈኑንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፡ ተደፍታችኹ ፡ ላሠራኹት ፡ ምስል ፡ ብትሰግዱ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ባትሰግዱ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ትጣላላችኹ ፤ ከእጄስ ፡ የሚያድናችኹ ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

16 ፤ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ መለሱ ፡ ንጉሡንም ፦ ናቡከደነጾር ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ እንመልስልኽ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊያችን ፡ አይደለም ።

17 ፤ የምናመልከው ፡ አምላካችን ፡ ከሚነደው ፡ ከእሳቱ ፡ እቶን ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ፤ ከእጅኽም ፡ ያድነናል ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ!

18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ ባያድነን ፥ አማልክትኽን ፡ እንዳናመልክ ፡ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንዳንሰግድለት ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ።

19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ናቡከደነጾር ፡ በሲድራቅና ፡ በሚሳቅ ፡ በዐብደናጎም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ሞላበት ፥ የፊቱም ፡ መልክ ፡ ተለወጠባቸው ፤ ርሱም ፡ ተናገረ ፥ የእቶንም ፡ እሳት ፡ ይነድ ፡ ከነበረው ፡ ይልቅ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርገው ፡ እንዲያነዱት ፡ አዘዘ ።

20 ፤ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅንም ፡ ዐብደናጎንም ፡ ያስሩ ፡ ዘንድ ፥ ወደሚነድም ፡ ወደእቶን ፡ እሳት ፡ ይጥሏቸው ፡ ዘንድ ፥ በሰራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ከነበሩት ፡ ኀያላን ፡ አዘዘ ።

21 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከሰናፊላቸውና ፡ ከቀሚሳቸው ፡ ከመጐናጸፊያቸውም ፡ ከቀረውም ፡ ልብሳቸው ፡ ጋራ ፡ ታስረው ፡ በሚነድ ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ተጣሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

22 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የእቶኑም ፡ እሳት ፡ እጅግ ፡ ስለሚነድ ፥ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ የጣሏቸውን ፡ ሰዎች ፡ የእሳቱ ፡ ወላፈን ፡ ገደላቸው ።

23 ፤ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ ታስረው ፡ በሚነደው ፡ በእቶኑ ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ወደቁ ።

24 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ተደነቀ ፡ ፈጥኖም ፡ ተነሣ ፤ አማካሪዎቹንም ፦ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ አስረን ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ጥለን ፡ አልነበረምን ፧ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። እነርሱም ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ መለሱለት ።

25 ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ የተፈቱ ፡ በእሳቱም ፡ መካከል ፡ የሚመላለሱ ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ አያለኹ ፤ ምንም ፡ አላቈሰላቸውም ፤ የአራተኛውም ፡ መልክ ፡ የአማልክትን ፡ ልጅ ፡ ይመስላል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

26 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደሚነደው ፡ ወደእሳቱ ፡ እቶን ፡ በር ፡ ቀርቦ ፦ እናንተ ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፥ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፥ ኑ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ሲድራቅና ፡ ሚሳቅም ፡ ዐብደናጎም ፡ ከእሳቱ ፡ መካከል ፡ ወጡ ።

27 ፤ መሳፍንቱና ፡ ሹማምቶቹም ፡ አዛገቹና ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪዎች ፡ ተሰብስበው ፡ እሳቱ ፡ በእነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ኀይል ፡ እንዳልነበረው ፥ የራሳቸውም ፡ ጠጕር ፡ እንዳልተቃጠለች ፥ ሰናፊላቸውም ፡ እንዳልተለወጠ ፥ የእሳቱም ፡ ሽታ ፡ እንዳልደረሰባቸው ፡ አዩ ።

28 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ መልሶ ፦ መልአኩን ፡ የላከ ፥ ከአምላካቸውም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አምላክ ፡ እንዳያመልኩ ፡ ለርሱም ፡ እንዳይሰግዱ ፡ ሰውነታቸውን ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡትን ፡ የንጉሡንም ፡ ቃል ፡ የተላለፉትን ፡ በርሱ ፡ የታመኑትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ያዳነ ፥ የሲድራቅና ፡ የሚሳቅ ፡ የዐብደናጎም ፡ አምላክ ፡ ይባረክ ።

29 ፤ እኔም ፡ እንደዚህ ፡ የሚያድን ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ በሲድራቅና ፡ በሚሳቅ ፡ በዐብደናጎም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ወገንና ፡ ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ይቈረጣሉ ፥ ቤቶቻቸውም ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረጋሉ ፡ ብዬ ፡ አዝዣለኹ ፡ አለ ።

30 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ ከንጉሡ ፡ ከናቡከደነጾር ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ወደሚቀመጡ ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ ወደሚናገሩ ፡ ኹሉ ፥ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

2 ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡ በፊቴ ፡ ያደረገውን ፡ ተኣምራቱንና ፡ ድንቁን ፡ አሳያችኹ ፡ ዘንድ ፡ ወድጃለኹ ።

3 ፤ ተኣምራቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! ድንቁም ፡ እንዴት ፡ ጽኑ ፡ ነው! መንግሥቱም ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፥ ግዛቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

4 ፤ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በቤቴ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ በአዳራሼም ፡ ተመችቶኝ ፡ ነበር ።

5 ፤ ሕልም ፡ ዐለምኹ ፤ ርሷም ፡ አስፈራችኝ ፤ በዐልጋዬም ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ዐሳቤና ፡ የራሴ ፡ ራእይ ፡ አስጨነቀኝ ።

6 ፤ ስለዚህ ፥ የሕልሙን ፡ ፍቺ ፡ እንዲያስታውቁኝ ፡ የባቢሎን ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኹ ።

7 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹና ፡ አስማተኞቹ ፡ ከለዳውያኑና ፡ ቃላተኞቹ ፡ ገቡ ፤ ሕልሙንም ፡ በፊታቸው ፡ ተናገርኹ ፥ ፍቺውን ፡ ግን ፡ አላስታወቁኝም ።

8 ፤ በመጨረሻም ፡ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ አምላኬ ፡ ስም ፡ ብልጣሶር ፡ የሚባለው ፡ ዳንኤል ፡ በፊቴ ፡ ገባ ፤ እኔም ፡ ሕልሙን ፡ ነገርኹት ፡ እንዲህም ፡ አልኹት ።

9 ፤ የሕልም ፡ ተርጓሚዎች ፡ አለቃ ፡ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡



www.ethiopianorthodox.org

እንዳለ ፥ ከምስጢርም ፡ ኹሉ ፡ የሚያስቸግርኽ ፡ እንደሌለ ፡ ዐውቄያለኹና ፡ ያለምኹትን ፡ የሕልሜን ፡ ራእይ ፡
ፍቺውንም ፡ ንገረኝ ።

10 ፤ የራሴ ፡ ራእይ ፡ በዐልጋዬ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እንሆ ፥ በምድር ፡ መካከል ፡ ዛፍ ፡ አየኹ ፥ ቁመቱም ፡ እጅግ ፡
ረዥም ፡ ነበረ ።

11 ፤ ዛፉም ፡ ትልቅ ፡ ኾነ ፥ በረታም ፥ ቁመቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ፥ መልኩም ፡ እስከምድር ፡ ኹሉ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡
ታየ ።

12 ፤ ቅጠሉም ፦ የተዋበ ፡ ነበረ ፡ ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነበረ ፥ ለኹሉም ፡ መብል ፡ ነበረበት ፤ ከጥላውም ፡ በታች ፡ የምድር ፡
አራዊት ፡ ያርፉበት ፡ ነበር ፥ በቅርንጫፎቹም ፡ ውስጥ ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፥ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ኹሉ ፡
ከርሱ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

13 ፤ በዐልጋዬም ፡ ላይ ፡ በራሴ ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ።

14 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ዛፉን ፡ ቍረጡ ፥ ቅርንጫፎቹንም ፡ ጨፍጭፉ ፥ ቅጠሎቹንም ፡
አራግፉ ፥ ፍሬውንም ፡ በትኑ ፤ አራዊትም ፡ ከበታቹ ፡ ወፎቹም ፡ ከቅርንጫፉ ፡ ይሽሹ ።

15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጕቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ተዉት ፥ በመስክም ፡ ውስጥ ፡ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡ ታስሮ ፡
ይቈይ ፤ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ይረስርስ ፡ ዕድል ፡ ፈንታውም ፡ በምድር ፡ ሣር ፡ ውስጥ ፡ ከአራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

16 ፤ ልቡም ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ይለወጥ ፥ የአውሬም ፡ ልብ ፡ ይሰጠው ፤ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ይለፉበት ።

17 ፤ ልዑሉ ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለወደደውም ፡ እንዲሰጠው ፥ ከሰውም ፡ የተዋረደውን ፡
እንዲሾምበት ፡ ሕያዋን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ የጠባቂዎች ፡ ትእዛዝ ፥ ይህም ፡ ፍርድ ፡ የቅዱሳን ፡ ቃል ፡ ነው ።

18 ፤ እኔ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይህን ፡ ሕልም ፡ ዐልሜያለኹ ፤ አንተም ፥ ብልጣሶር ፥ ፍቹውን ፡
አስታውቀኝ ፥ የመንግሥቴ ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ፍቹውን ፡ ያስታውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የቅዱሳን ፡
አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ አለና ፡ አንተ ፡ ትችላለኽ ።

19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብልጣሶር ፡ የተባለው ፡ ዳንኤል ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ዐሰበ ፥ ልቡም ፡ ታወከ ። ንጉሡም ፡
መልሶ ፦ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ ሕልሙና ፡ ፍቺው ፡ አያስቸግርኽ ፡ አለው ። ብልጣሶርም ፡ መልሶ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡
ሆይ ፥ ሕልሙ ፡ ለሚጠሉኽ ፥ ፍቺውም ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ይኹን ።

20 ፤ ትልቅ ፡ የነበረው ፡ የበረታውም ፥ ቁመቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የደረሰው ፥ መልኩም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ድረስ ፡
የታየው ፥

21 ፤ ቅጠሉም ፡ አምሮ ፡ የነበረው ፥ ፍሬውም ፡ የበዛው ፥ ለኹሉም ፡ መብል ፡ የነበረበት ፤ በበታቹም ፡ የምድር ፡ አራዊት ፡
የተቀመጡ ፥ በቅርንጫፎቹም ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ያደሩበት ፡ ያየኸው ፡ ዛፍ ፤

22 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ የኾንኽ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፤ ታላቅነትኽ ፡ በዝቷል ፥ እስከ ፡ ሰማይም ፡
ደርሷል ፥ ግዛትኽም ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

23 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰማይ ፡ የወረደውንና ፦ ዛፉን ፡ ቍረጡ ፥ አጥፉትም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጕቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡
ተዉት ፤ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡ ታስሮ ፡ በመስክ ፡ ውስጥ ፡ ይቈይ ፤ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ይረስርስ ፥ ሰባት ፡
ዘመናትም ፡ እስኪያልፉበት ፡ ድረስ ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፡ ያለውን ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡
ማየቱ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ፍቺው ፡ ይህ ፡ ነው ፤

24 ፤ በጌታዬ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ የወረደው ፡ የልዑሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፤

25 ፤ ልዑሉም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለሚወድውም ፡ እንዲሰጠው ፡ እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡
ከሰዎች ፡ ተለይተኽ ፡ ትሰደዳለኽ ፥ መኖሪያኽም ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፥ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ ትበላ ፡
ዘንድ ፡ ትገደዳለኽ ፥ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ትረሰርሳለኽ ፥ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ያልፉብኻል ።

26 ፤ የዛፉንም ፡ ጕቶ ፡ ይተዉት ፡ ዘንድ ፡ ማዘዙ ፥ ሥልጣን ፡ ከሰማያት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ካወቅኽ ፡ በኋላ ፡ መንግሥትኽ ፡
ይቈይልኻል ።



www.ethiopianorthodox.org

27 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ የደኅንነትኽ ፡ ዘመን ፡ ይረዝም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምክሬ ፡ ደስ ፡
ያሠኝኽ ፤ ኀጢአትኽንም ፡ በጽድቅ ፥ በደልኽንም ፡ ለድኻዎች ፡ በመመጽወት ፡ አስቀር ።

28 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡ ደረሰ ።

29 ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

30 ፤ ንጉሡም ፦ ይህች ፡ እኔ ፡ በጒልበቴ ፡ ብርታት ፡ ለግርማዬ ፡ ክብር ፡ የመንግሥት ፡ መኖሪያ ፡ እንድትኾን ፡
ያሠራኋት ፡ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ አይደለችምን ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

31 ፤ ቃሉም ፡ ገና ፡ በንጉሡ ፡ አፍ ፡ ሳለ ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀና ፦ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ሆይ ፦ መንግሥት ፡
ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ዐለፈች ፡ ተብሎ ፡ ለአንተ ፡ ተነግሯል ፤

32 ፤ ልዑሉም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለሚወደውም ፡ እንዲሰጠው ፡ እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡
ከሰዎች ፡ ተለይተኽ ፡ ትሰደዳለኽ ፥ መኖሪያኽም ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፤ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ ትበላ ፡
ዘንድ ፡ ትገደዳለኽ ፥ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ያልፉብኻል ፡ አለው ።

33 ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ነገሩ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡ ደረሰ ፤ ጠጒሩም ፡ እንደ ፡ ንስር ፥ ጥፍሩም ፡ እንደ ፡ ወፎች ፡
እስኪረዝም ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ተሰደደ ፥ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ በላ ፥ አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ።

34 ፤ ዘመኑም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ዐይኔን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አነሣኹ ፥ አእምሮዬም ፡
ተመለሰልኝ ፤ ልዑሉንም ፡ ባረክኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ የሚኖረውን ፡ አመሰገንኹ ፡ አከበርኹትም ፤ ግዛቱ ፡ የዘለዓለም ፡
ግዛት ፡ ነውና ፥ መንግሥቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ።

35 ፤ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ ይቈጠራሉ ፤ በሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ በሚኖሩ ፡
መካከል ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፤ እጁንም ፡ የሚከለክላት ፡ ወይም ፦ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፡ የሚለው ፡ የለም ።

36 ፤ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ አእምሮዬ ፡ ተመለሰልኝ ፥ ለመንግሥቴም ፡ ክብር ፡ ግርማዬና ፡ ውበቴ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
ተመለሰ ፤ አማካሪዎቼና ፡ መኳንንቶቼም ፡ ፈለጉኝ ፥ በመንግሥቴም ፡ ውስጥ ፡ ጸናኹ ፥ ብዙም ፡ ክብር ፡ ተጨመረልኝ ።

37 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የሰማይን ፡ ንጉሥ ፡ አመሰግናለኹ ፥ ታላቅም ፡
አደርገዋለኹ ፥ አከብረውማለኹ ። ሥራው ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፥ መንገዱም ፡ ፍርድ ፡ ነውና ፥ በትዕቢትም ፡ የሚኼዱትን ፡
ያዋርድ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልና ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምዕራፍ ፡ 5 ።

1 ፤ ንጉሡ ፡ ብልጣሶር ፡ ለሺሕ ፡ መኳንንቶቹ ፡ ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፥ በሺሑም ፡ ፊት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣ ፡
ነበር ።

2 ፤ ብልጣሶርም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንንቶቹ ፣ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹ ፡ ይጠጡባቸው ፡
ዘንድ ፦ አባቴ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ መቅደስ ፡ ያመጣቸውን ፡ የወርቁንና ፡ የብሩን ፡ ዕቃዎች ፡
አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

3 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የመጡትን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃዎች ፡
አመጡ ፤ ንጉሡና ፡ መኳንንቶቹም ፡ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹም ፡ ጠጡባቸው ።

4 ፤ የወይን ፡ ጠጅም ፡ እየጠጡ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፣ ከናስና ፡ ከብረት ፣ ከዕንጨትና ፡ ከድንጋይ ፡ የተሠሩትን ፡
አማልክት ፡ አመሰገኑ ።

5 ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ጣቶች ፡ ወጥተው ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ በተለሰነው ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ በመቅረዙ ፡ አንጻር ፡
ጻፉ ፤ ንጉሡም ፡ የሚጽፉትን ፡ ጣቶች ፡ አየ ።

6 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሡ ፡ ፊት ፡ ተለወጠበት ፥ ዐሳቡም ፡ አስቸገረው ፥ የወገቡም ፡ ኾማቶች ፡
ተፈቱ ፥ ጒልበቶቹም ፡ ተብረከረኩ ።



www.ethiopianorthodox.org

7 ፤ ንጉሡም ፡ አስማተኛዎቹንና ፡ ከለዳውያኑን ፣ ቃላተኛዎቹንም ፡ ያገቡ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ፤ ንጉሡም ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፦ ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ ያነበበ ፥ ፍቺውንም ፡ ያሳየኝ ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ይለብሳል ፥ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በዐንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ ይኾንለታል ፥ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሡ ፡ ጠቢባን ፡ ዅሉ ፡ ገቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽሕፈቱን ፡ ያነቡ ፥ ፍቺውንም ፡ ለንጉሡ ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

9 ፤ ንጉሡም ፡ ብልጣሶር ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ፥ ፊቱም ፡ ተለወጠበት ፥ መኳንንቶቹም ፡ ተደናገጡ ።

10 ፤ ንግሥቲቱም ፡ ስለንጉሡና ፡ ስለመኳንንቱ ፡ ቃል ፡ ወደግብዣ ፡ ቤት ፡ ገባች ፤ ንግሥቲቱም ፡ ተናገረች ፥ እንዲህም ፡ አለች ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ ዐሳብኽ ፡ አያስቸግርኽ ፥ ፊትኽም ፡ አይለወጥ ።

11 ፤ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በመንግሥትኽ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፤ በአባትኽም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አማልክት ፡ ጥበብ ፡ ያለ ፡ ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ ዕውቀትም ፡ ተገኘበት ፤ አባትኽ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ የአስማተኛዎች ፣ የከለዳውያንና ፡ የቃላተኛዎች ፡ አለቃ ፡ አደረገው ።

12 ፤ መልካም ፡ መንፈስ ፣ ዕውቀትም ፣ ማስተዋልም ፣ ሕልምንም ፡ መተርጐም ፥ እንቆቅልሽንም ፡ መግለጥ ፥ የተቋጠረውንም ፡ መፍታት ፡ ንጉሡ ፡ ስሙን ፡ ብልጣሶር ፡ ብሎ ፡ በሰየመው ፡ በዳንኤል ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷልና ። አኹንም ፡ ዳንኤል ፡ ይጠራ ፥ ርሱም ፡ ፍቺውን ፡ ያሳያል ።

13 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደንጉሡ ፡ ፊት ፡ ገባ ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረው ፥ ዳንኤልንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ንጉሡ ፡ አባቴ ፡ ከይሁዳ ፡ ከማረካቸው ፣ ከይሁዳ ፡ ምርኮኛዎች ፡ የኾንኽ ፡ ዳንኤል ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧

14 ፤ የአማልክት ፡ መንፈስ ፡ እንዳለብኽ ፥ ዕውቀትና ፡ ማስተዋልም ፣ መልካምም ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ተገኘብኽ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ሰምቻለኹ ።

15 ፤ አኹንም ፡ ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ ያነቡ ፡ ዘንድ ፥ ፍቺውንም ፡ ያስታውቁኝ ፡ ዘንድ ፥ ጠቢባንና ፡ አስማተኛዎች ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ገብተው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የነገሩን ፡ ፍቺ ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

16 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ፍቺን ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፥ የተቋጠረንም ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ እንድትችል ፡ ሰምቻለኹ ፤ አኹንም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ታነብ ፡ ዘንድ ፥ ፍቺውንም ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ብትችል ፥ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ትለብሳለኽ ፥ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በዐንገትኽ ፡ ዙሪያ ፡ ይኾንልኻል ፥ አንተም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ ትኾናለኽ ።

17 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ መለሰ ፥ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ስጦታኽ ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፥ በረከትኽንም ፡ ለሌላ ፡ ስጥ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽሕፈቱን ፡ ለንጉሡ ፡ አነባለኹ ፥ ፍቺውንም ፡ አስታውቃለኹ ።

18 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ለአባትኽ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ መንግሥትንና ፡ ታላቅነትን ፣ ክብርንና ፡ ግርማን ፡ ሰጠው ።

19 ፤ ስለሰጠው ፡ ታላቅነት ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፣ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ዅሉ ፡ በፊቱ ፡ ይንቀጠቀጡና ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ፤ የፈቀደውን ፡ ይገድል ፥ የፈቀደውንም ፡ በሕይወት ፡ ያኖር ፡ ነበር ፤ የፈቀደውንም ፡ ያነሣ ፥ የፈቀደውንም ፡ ያዋርድ ፡ ነበር ።

20 ፤ ልቡ ፡ ግን ፡ በታበየ ፥ በኵራትም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሱ ፡ በጠነከረ ፡ ጊዜ ፥ ከመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ተዋረደ ፥ ክብሩም ፡ ተለየው ።

21 ፤ ልዑል ፡ አምላክም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ የሚወደውንም ፡ እንዲሾምበት ፡ እስኪያውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ተይለቶ ፡ ተሰደደ ፤ ልቡም ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ልብ ፡ ኾነ ፥ መኖሪያውም ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ አህያዎች ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ እንደ ፡ በሬ ፡ ሣር ፡ በላ ፥ አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ።

22 ፤ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ልጁ ፡ ስትኾን ፡ ይህን ፡ ዅሉ ፡ እያወቅኽ ፡ በሰማይ ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ ኰራኽ ፡ እንጂ ፡ ልብኽን ፡ አላዋረድኽም ።

23 ፤ የመቅደሱንም ፡ ዕቃዎች ፡ በፊትኽ ፡ አመጡ ፥ አንተም ፣ መኳንንትኽም ፣ ሚስቶችኽም ፣ ቁባቶችኽም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣችኹባቸው ፤ ከብርና ፡ ከወርቅም ፣ ከናስና ፡ ከብረትም ፣ ከዕንጨትና ፡ ከድንጋይም ፡



www.ethiopianorthodox.org

የተሠሩትን ፥ የማያዩትንም ፥ የማይሰሙትንም ፥ የማያውቁትንም ፡ አማልክት ፡ አመሰገንኽ ፤ ትንፋሽኽንና ፡ መንገድኽን ፡ ኹሉ ፡ በእጁ ፡ የያዘውን ፡ አምላክ ፡ አላከበርኽውም ።

24 ፤ ስለዚህም ፡ እነዚህ ፡ የእጅ ፡ ጣቶች ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተልከዋል ፤ ይህም ፡ ጽሕፈት ፡ ተጽፏል ።

25 ፤ የተጻፈውም ፡ ጽሕፈት ፦ ማኔ ፡ ቴቄል ፡ ፋሬስ ፡ ይላል ።

26 ፤ የነገሩም ፡ ፍቺ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ማኔ[267] ፡ ማለት ፥ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትኽን ፡ ቈጠረው ፥ ፈጸመውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

27 ፤ ቴቄል[268] ፡ ማለት ፥ በሚዛን ፡ ተመዘንኽ ፥ ቀልኽም ፡ ተገኘኽ ፡ ማለት ፡ ነው ።

28 ፤ ፋሬስ[269] ፡ ማለት ፥ መንግሥትኽ ፡ ተከፈለ ፥ ለሜዶንና ፡ ለፋርስ ፡ ሰዎችም ፡ ተሰጠ ፡ ማለት ፡ ነው ።

29 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብልጣሶር ፡ ለዳንኤል ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ እንዲያለብሱት ፥ የወርቅ ፡ ማርዳም ፡ በዐንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ እንዲያደርጉለት ፡ አዘዘ ፤ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ እንዲኾን ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ።

30 ፤ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ የከለዳውያን ፡ ንጉሥ ፡ ብልጣሶር ፡ ተገደለ ።

31 ፤ ሜዶናዊውም ፡ ዳርዮስ ፡ መንግሥቱን ፡ ወሰደ ፤ ዕድሜውም ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምዕራፍ ፡ 6 ።

1 ፤ ዳርዮስም ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲኾኑ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መሳፍንት ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።

2 ፤ መሳፍንቱም ፡ ሒሳቡን ፡ ያመጡላቸው ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡም ፡ እንዳይጐዳ ፥ ሦስት ፡ አለቃዎች ፡ በላያቸው ፡ አደረገ ፤ ከነርሱም ፡ አንደኛው ፡ ዳንኤል ፡ ነበረ ።

3 ፤ ዳንኤልም ፡ መልካም ፡ መንፈስ ፡ ስለ ፡ አለው ፥ ከአለቃዎችና ፡ ከመሳፍንት ፡ በለጠ ፤ ንጉሡም ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመው ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

4 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አለቃዎችና ፡ መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሰበብ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የታመነ ፡ ነበረና ፥ ስሕተትና ፡ በደልም ፡ አልተገኘበትምና ፥ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሰበብና ፡ በደል ፡ ያገኙበት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

5 ፤ እነዚያም ፡ ሰዎች ፦ ከአምላኩ ፡ ሕግ ፡ በቀር ፥ በዚህ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰበብ ፡ አናገኝበትም ፡ አሉ ።

6 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አለቃዎቹና ፡ መሳፍንቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰብስበው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

7 ፤ የመንግሥቱ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፤ ሹማምቶችና ፡ መሳፍንት ፤ አማካሪዎችና ፡ አዛገሮች ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልመና ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ቢለምን ፥ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይጣል ፥ የሚል ፡ የንጉሥ ፡ ሕግና ፡ ብርቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ።

8 ፤ አኹንም ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እንደማይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡ ሕግ ፥ እንዳይለወጥ ፡ ትእዛዙን ፡ አጽና ፥ ጽሕፈቱንም ፡ ጻፍ ።

9 ፤ ንጉሡም ፡ ዳርዮስ ፡ ጽሕፈቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ጻፈ ።

10 ፤ ዳንኤልም ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፤ የዕልፍኙም ፡ መስኮቶች ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ አንጻር ፡ ተከፍተው ፡ ነበር ፤ ቀድሞም ፡ ያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ በየዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ በአምላኩ ፡ ፊት ፡ ጸለየ ፥ አመሰገነም ።

---

267 ሱር. ፥ ምናህ ፡ (ሰፈረ ፥ ቈጠረ ፥ ፈጸመ ፤ ኪ..ወ.ክ.598) ።
268 ሱር. ፥ ትቄል ፡ (ሰቀለ ፥ ደለወ ፥ መዘነ ፤ ኪ..ወ.ክ.902) ።
269 ሱር. ፥ ፋርሲን ፡ (ከፈል • ፍራሽ) ።



www.ethiopianorthodox.org

11 ፤ እነዚያም ፥ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፥ ዳንኤል ፡ በአምላኩ ፡ ፊት ፡ ሲጸልይና ፡ ሲለምን ፡ አገኙት ።

12 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ቀርበው ፥ ስለንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ የሚለምን ፡ ሰው ፡ ሹሉ ፡ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጣል ፡ ትእዛዝ ፡ አልጻፍኽምን ፧ አሉት ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ነገሩ ፡ እንደማይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡ ሕግ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አላቸው ።

13 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሰው ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ የኾነው ፡ ዳንኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ልመናውን ፡ ይለምናል ፡ እንጂ ፥ አንተንና ፡ የጻፍኸውን ፡ ትእዛዝ ፡ አይቀበልም ፡ አሉት ።

14 ፤ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ዐዘነ ፥ ያድነውም ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ አደረገ ፤ ሊያድነውም ፡ ፀሓይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ደከመ ።

15 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰብስበው ፡ ንጉሡን ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ንጉሡ ፡ ያጸናው ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ሥርዐት ፡ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባ ፡ የሜዶንና ፡ የፋርስ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ።

16 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ አዘዘ ፥ ዳንኤልንም ፡ አምጥተው ፡ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ጣሉት ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረ ፥ ዳንኤልንም ፦ ኹልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክኽ ፡ ርሱ ፡ ያድንኽ ፡ አለው ።

17 ፤ ድንጋይም ፡ አምጥተው ፡ በጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ገጠሙበት ፤ ንጉሡም ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ እንዳይለወጥ ፡ በቀለበቱና ፡ በመኳንንቱ ፡ ቀለበት ፡ አተመው ።

18 ፤ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፥ ሳይበላም ፡ ዐደረ ፤ መብልም ፡ አላመጡለትም ፥ እንቅልፉም ፡ ከርሱ ፡ ራቀ ።

19 ፤ በነጋውም ፡ ንጉሡ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ፈጥኖም ፡ ወዳንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ኼደ ።

20 ፤ ወደ ፡ ጕድጓዱም ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፥ በሐዘን ፡ ቃል ፡ ጠራው ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረ ፥ ዳንኤልንም ፦ የሕያው ፡ አምላክ ፡ ባሪያ ፡ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ኹልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክኽ ፡ ከአንበሳዎች ፡ ያድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ችሏልን ፧ አለው ።

21 ፤ ዳንኤልም ፡ ንጉሡን ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

22 ፤ በፊቱ ፡ ቅንነት ፡ ተገኝቶብኛልና ፥ ባንተም ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አልበደልኹምና ፥ አምላኬ ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ የአንበሳዎችን ፡ አፍ ፡ ዘጋ ፥ እነርሱም ፡ አልጐዱኝም ፡ አለው ።

23 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ዳንኤልንም ፡ ከጕድጓዱ ፡ ያወጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ዳንኤልም ፡ ከጕድጓድ ፡ ወጣ ፥ በአምላኩም ፡ ታምኖ ፡ ነበርና ፥ አንዳች ፡ ጕዳት ፡ አልተገኘበትም ።

24 ፤ ንጉሡም ፡ አዘዘ ፥ ዳንኤልንም ፡ የከሰሱ ፡ እነዚያን ፡ ሰዎች ፡ አመጧቸው ፥ እነርሱንና ፡ ልጆቻቸውንም ፣ ሚስቶቻቸውንም ፡ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ጣሏቸው ፤ ወደጕድጓዱም ፡ መጨረሻ ፡ ሳይደርሱ ፡ አንበሳዎች ፡ ያዟቸው ፥ ዐጥንታቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ሰባበሩ ።

25 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወደሚኖሩ ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፥ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ ወደሚናገሩ ፡ ኹሉ ፡ ጻፈ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

26 ፤ በመንግሥቴ ፡ ግዛት ፡ ኹሉ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በዳንኤል ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ እንዲፈሩና ፡ እንዲንቀጠቀጡ ፡ አዝዣለኹ ፤ ርሱ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ነውና ፤ መንግሥቱም ፡ የማይጠፋ ፡ ነው ፥ ግዛቱም ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ይኖራል ።

27 ፤ ያድናል ፥ ይታደግማል ፤ በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ተኣምራትንና ፡ ድንቅን ፡ ይሠራል ፤ ዳንኤልንም ፡ ከአንበሳዎች ፡ አፍ ፡ አድኖታል ።

28 ፤ ይህም ፡ ዳንኤል ፡ በዳርዮስ ፡ መንግሥትና ፡ በፋርሳዊው ፡ በቂሮስ ፡ መንግሥት ፡ ኑሮው ፡ ተቃናለት ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምዕራፍ ፡ 7 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በብልጣሶር ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ ዳንኤል ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ሕልምንና ፡ የራሱን ፡ ራእይ ፡ አየ ፤ ከዚያም ፡ በ'ዃላ ፡ ሕልሙን ፡ ጻፈ ፥ ዋነኛውንም ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

2 ፤ ዳንኤልም ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ በሌሊት ፡ በራእይ ፡ አየ'ኹ ፤ እንሆም ፥ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ በታላቁ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ይጋጩ ፡ ነበር ።

3 ፤ አራትም ፡ ታላላቅ ፡ አራዊት ፡ ከባሕር ፡ ወጡ ፥ እያንዳንዲቱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነበረች ።

4 ፤ መዠመሪያዪቱ ፡ አንበሳ ፡ ትመስል ፡ ነበር ፥ የንስርም ፡ ክንፍ ፡ ነበራት ፤ ክንፎቿም ፡ ከርሷ ፡ እስኪነቀሉ ፡ ድረስ ፡ አይ ፡ ነበር ፥ ከምድርም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ተደረገች ፥ እንደ ፡ ሰውም ፡ በ'ኹለት ፡ እግር ፡ እንድትቆም ፡ ተደረገች ፥ የሰውም ፡ ልብ ፡ ተሰጣት ።

5 ፤ እንሆም ፥ 'ኹለተኛዪቱ ፡ ድብ ፡ የምትመስል ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ ነበረች ፥ ባንድ ፡ ወገንም ፡ ቆመች ፥ ሦስትም ፡ የጐድን ፡ ዐጥንቶች ፡ በአፏ ፡ ውስጥ ፡ በጥርሷ ፡ መካከል ፡ ነበሩ ፤ እንደዚህም ፦ ተነሥተሽ ፡ እጅግ ፡ ሥጋ ፡ ብዪ ፡ ተባለላት ።

6 ፤ ከዚህም ፡ በ'ዃላ ፥ እንሆ ፥ ነብር ፡ የምትመስል ፡ በዠርባዋም ፡ ላይ ፡ አራት ፡ የወፍ ፡ ክንፎች ፡ የነበሯት ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ አየ'ኹ ፤ ለአውሬዪቱም ፡ አራት ፡ ራሶች ፡ ነበሯት ፥ ግዛትም ፡ ተሰጣት ።

7 ፤ ከዚህም ፡ በ'ዃላ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ አየ'ኹ ፤ እንሆም ፥ የምታስፈራና ፡ የምታስደነግጥ ፡ እጅግም ፡ የበረታች ፥ ታላላቅም ፡ የብረት ፡ ጥርሶች ፡ የነበሯት ፡ አራተኛ ፡ አውሬ ፡ ነበረች ፤ ትበላና ፡ ታደቅ ፡ ነበር ፥ የቀረውንም ፡ በእግሯ ፡ ትረግጥ ፡ ነበር ፤ ከርሷም ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ አራዊት ፡ 'ኹሉ ፡ የተለየች ፡ ነበረች ፤ ዐሥር ፡ ቀንዶችም ፡ ነበሯት ።

8 ፤ ቀንዶችንም ፡ ተመለከት'ኹ ፤ እንሆም ፥ በመካከላቸው ፡ ሌላ ፡ ትንሽ ፡ ቀንድ ፡ ወጣ ፥ በፊቱም ፡ ከቀደሙት ፡ ቀንዶች ፡ ሦስት ፡ ተነቃቀሉ ፤ እንሆም ፥ በዚያ ፡ ቀንድ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዐይኖች ፡ የነበሩ ፡ ዐይኖች ፡ በትዕቢትም ፡ የሚናገር ፡ አፍ ፡ ነበሩበት ።

9 ፤ ዙፋኖችም ፡ እስኪዘረጉ ፡ ድረስ ፡ አየ'ኹ ፥ በዘመናት ፡ የሸመገለውም ፡ ተቀመጠ ፤ ልብሱም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፥ የራሱም ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ ጥሩ ፡ ጥጥ ፡ ነበረ ፤ ዙፋኑም ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ነበረ ፥ መንኰራኵሮቹም ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡ ነበሩ ።

10 ፤ የእሳትም ፡ ፈሳሽ ፡ ከፊቱ ፡ ይፈልቅና ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፤ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ ያገለግሉት ፡ ነበር ፥ እልፍ ፡ አእላፋትም ፡ በፊቱ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ፍርድም ፡ 'ኾነ ፥ መጻሕፍትም ፡ ተገለጡ ።

11 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቀንዱ ፡ ይናገረው ፡ ከነበረው ፡ ከታላቁ ፡ ቃል ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ አየ'ኹ ፤ አውሬዪቱም ፡ እስክትገደል ፥ አካሏም ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፥ በእሳትም ፡ ለመቃጠል ፡ እስክትሰጥ ፡ ድረስ ፡ አየ'ኹ ።

12 ፤ ከቀሩትም ፡ አራዊት ፡ ግዛታቸው ፡ ተወሰደ ፤ የሕይወታቸው ፡ ዕድሜ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዘመንና ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ረዘመ ።

13 ፤ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ አየ'ኹ ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ከሰማይ ፡ ደመናት ፡ ጋራ ፡ መጣ ፡ በዘመናት ፡ ወደሸመገለውም ፡ ደረሰ ፤ ወደ ፡ ፊቱም ፡ አቀረቡት ።

14 ፤ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የሚናገሩ ፡ 'ኹሉ ፡ ይገዙለት ፡ ዘንድ ፡ ግዛትና ፡ ክብር ፡ መንግሥትም ፡ ተሰጠው ፤ ግዛቱም ፡ የማያልፍ ፡ የዘለዓለም ፡ ግዛት ፡ ነው ፥ መንግሥቱም ፡ የማይጠፋ ፡ ነው ።

15 ፤ በእኔም ፡ በዳንኤል ፡ በሥጋዬ ፡ ውስጥ ፡ መንፈሴ ፡ ደነገጠች ፥ የራሴም ፡ ራእይ ፡ አስቸገረኝ ።

16 ፤ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቀርቤ ፡ ስለዚህ ፡ 'ኹሉ ፡ እውነቱን ፡ ጠየቅ'ኹት ፤ ርሱም ፡ ነገረኝ ፥ የነገሩንም ፡ ፍቺ ፡ አስታወቀኝ ።

17 ፤ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ታላላቅ ፡ አራዊት ፡ ከምድር ፡ የሚነሡ ፡ አራት ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።

18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ መንግሥቱን ፡ ይወስዳሉ ፥ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ዓለምም ፡ መንግሥቱን ፡ ይወርሳሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

19 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከቀሩት ፡ ኹሉ ፡ ተለይታ ፡ እጅግ ፡ ስለምታስፈራው ፥ ጥርሶቿም ፡ የብረት ፡ ጥፍራዎቿም ፡ የናስ ፡ ስለ ኾኑት ፥ ስለምትበላውና ፡ ስለምታደቅው ፡ የቀረውንም ፡ በእግሯ ፡ ስለምትረግጠው ፡ ስለ ፡ አራተኛዪቱ ፡ አውሬ ፥

20 ፤ በራሷም ፡ ላይ ፡ ስለነበሩ ፡ ስለ ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶች ፥ በኋላም ፡ ስለ ፡ ወጣው ፥ በፊቱም ፡ ሦስቱ ፡ ስለ ፡ ወደቁ ፥ ዐይኖችና ፡ ትዕቢት ፡ የተናገረ ፡ አፍ ፡ ስለ ፡ ነበሩት ፥ መልኩም ፡ ከሌላዎች ፡ ስለ ፡ በለጠ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ ቀንድ ፡ እውነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈቀድኹ ።

21 ፤ እንሆም ፥ ያ ፡ ቀንድ ፡ ከቅዱሳን ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ አየኹ ፥

22 ፤ በዘመናት ፡ የሸመገለው ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፥ ፍርድም ፡ ለልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፥ ቅዱሳኑም ፡ መንግሥቱን ፡ የሚወስዱበት ፡ ዘመን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አሸነፋቸውም ።

23 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አራተኛዪቱ ፡ አውሬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አራተኛ ፡ መንግሥት ፡ ትኾናለች ፤ ርሱም ፡ ከመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ የተለየ ፡ ይኾናል ፥ ምድሪቱንም ፡ ኹሉ ፡ ይበላል ፥ ይረግጣታል ፡ ያደቅትማል ።

24 ፤ ዐሥሩም ፡ ቀንዶች ፡ ከዚያ ፡ መንግሥት ፡ የሚነሡ ፡ ዐሥር ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ይነሣል ፥ ርሱም ፡ ከፊተኛዎች ፡ የተለየ ፡ ይኾናል ፥ ሦስቱንም ፡ ነገሥታት ፡ ያዋርዳል ።

25 ፤ በልዑሉም ፡ ላይ ፡ ቃልን ፡ ይናገራል ፥ የልዑልንም ፡ ቅዱሳን ፡ ይሰባብራል ፥ ዘመናትንና ፡ ሕግን ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ያስባል ፤ እስከ ፡ ዘመንና ፡ እስከ ፡ ዘመናት ፡ እስከ ፡ እኩሌታ ፡ ዘመንም ፡ በእጁ ፡ ይሰጣሉ ።

26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፍርድ ፡ ይኾናል ፥ እስከ ፡ ፍጻሜም ፡ ድረስ ፡ ያፈርሱትና ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ ግዛቱን ፡ ያስወግዱታል ።

27 ፤ መንግሥትም ፡ ግዛትም ፡ ከሰማይም ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ የመንግሥታት ፡ ታላቅነት ፡ ለልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሕዝብ ፡ ይሰጣል ፤ መንግሥቱ ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፥ ግዛቶችም ፡ ኹሉ ፡ ይገዙለታል ፡ ይታዘዙለትማል ።

28 ፤ የነገሩም ፡ ፍጻሜ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ። እኔም ፡ ዳንኤል ፡ በዐሳቤ ፡ እጅግ ፡ ተቸገርኹ ፥ ፊቴም ፡ ተለወጠብኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ በልቤ ፡ ጠብቄያለኹ ።

__________________ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 8 ።

1 ፤ በመዠመሪያ ፡ ከተገለጠልኝ ፡ ራእይ ፡ በኋላ ፥ ንጉሡ ፡ ብልጣሶር ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፥ ለእኔ ፡ ለዳንኤል ፡ ራእይ ፡ ተገለጠልኝ ።

2 ፤ በራእዩም ፡ አየኹ ፤ ባየኹም ፡ ጊዜ ፡ በዔላም ፡ አውራጃ ፡ ባለው ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ነበርኹ ፤ በራእዩም ፡ አየኹ ፡ በኡባል ፡ ወንዝም ፡ አጠገብ ፡ ነበርኹ ።

3 ፤ ዐይኔን ፡ አንሥቼ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ቀንዶች ፡ የነበሩት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ በወንዙ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ ኹለቱም ፡ ቀንዶቹ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፤ አንዱ ፡ ግን ፡ ከኹለተኛው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበረ ፥ ታላቁም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ።

4 ፤ አውራውም ፡ በግ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ በቀንዱ ፡ ሲጐሽም ፡ አየኹ ፤ አራዊትም ፡ ኹሉ ፡ ይቋቋሙት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፥ ከእጁም ፡ የሚያድን ፡ አልነበረም ፤ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ አደረገ ፥ ራሱንም ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ።

5 ፤ እኔም ፡ ስመለከት ፥ እንሆ ፥ ከምዕራብ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ምድርንም ፡ አልነካም ፤ ለፍየሉም ፡ በዐይኖቹ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ቀንድ ፡ ነበረው ።

6 ፤ ኹለትም ፡ ቀንድ ፡ ወዳለው ፡ በወንዝም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ወዳየኹት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ መጣ ፥ በኀይሉም ፡ ቍጣ ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሮጠ ።

7 ፤ ወደ ፡ አውራውም ፡ በግ ፡ ሲቀርብ ፡ አየኹት ፤ ርሱም ፡ ተመረረበት ፥ አውራውንም ፡ በግ ፡ መታ ፥ ኹለቱንም ፡ ቀንዶች ፡ ሰበረ ፤ አውራውም ፡ በግ ፡ ሊቋቋመው ፡ ኀይል ፡ አልነበረውም ፥ ርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ረገጠው ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ ከእጁ ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ።



www.ethiopianorthodox.org

8 ፤ አውራውም ፡ ፍየል ፡ ራሱን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ፤ በበረታም ፡ ጊዜ ፡ ታላቁ ፡ ቀንዱ ፡ ተሰበረ ፥ ወደ ፡ አራቱም ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ የሚመለከቱ ፡ አራት ፡ ቀንዶች ፡ ከበታቹ ፡ ወጡ ።

9 ፤ ከነርሱም ፡ ከአንደኛው ፡ አንድ ፡ ታናሽ ፡ ቀንድ ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ወደ ፡ መልካሚቱም ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

10 ፤ እስከሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ከሰራዊትና ፡ ከከዋክብትም ፡ ዐያሌዎችን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለ ፥ ረገጣቸውም ።

11 ፤ እስከሰራዊትም ፡ አለቃ ፡ ድረስ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ፤ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ የዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፡ ተሻረ ፥ የመቅደሱም ፡ ስፍራ ፡ ፈረሰ ።

12 ፤ ሰራዊቱም ፡ ከኀጢአት ፡ የተነሣ ፡ ከዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ ተሰጠው ፤ ርሱም ፡ እውነትን ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ጣለ ፥ አደረገም ፡ ተከናወነም ።

13 ፤ ከቅዱሳኑም ፡ አንዱ ፡ ሲናገር ፡ ሰማኹ ፤ ለተናገረው ፡ ለቅዱሱም ፡ ኹለተኛው ፡ ቅዱስ ፦ ስለዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፥ መቅደሱና ፡ ሰራዊቱም ፡ ይረገጡ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚሰጥና ፡ ስለሚያጠፋ ፡ ኀጢአት ፡ የኾነው ፡ ራእይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይኾናል ፡፡ አለው ።

14 ፤ ርሱም ፦ እስከ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ማታና ፡ ጧት ፡ ድረስ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ መቅደሱ ፡ ይነጻል ፡ አለኝ ።

15 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ራእዩን ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ ማስተዋሉን ፡ ፈለግኹ ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ምስያ ፡ በፊቴ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

16 ፤ በኡባልም ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፦ ገብርኤል[270] ፡ ሆይ ፥ ራእዩን ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ አስታውቀው ፡ ብሎ ፡ የሚጮኽውን ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

17 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ቆምኹበት ፡ ቀረበ ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ፈርቼ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ራእዩ ፡ ለፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፡ አለኝ ።

18 ፤ ሲናገረኝም ፡ ደንግጬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ፤ ርሱም ፡ ዳሰሰኝ ፡ ቀጥ ፡ አድርጎም ፡ አቆመኝ ።

19 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ እንሆ ፥ በመቅሠፍቱ ፡ በመጨረሻ ፡ ዘመን ፡ የሚኾነውን ፡ አስታውቅኻለኹ ፤ ይህ ፡ ለተወሰነው ፡ ለፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ነውና ።

20 ፤ ባየኸው ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ ኹለቱ ፡ ቀንዶች ፡ እነርሱ ፡ የሜዶንና ፡ የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።

21 ፤ አውራውም ፡ ፍየል ፡ የግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ በዐይኖቹም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡ ቀንድ ፡ መዠመሪያው ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

22 ፤ ርሱም ፡ በተሰበረ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አራቱ ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፥ እንዲሁ ፡ ከወገኑ ፡ አራት ፡ መንግሥታት ፡ ይነሣሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በኀይል ፡ አይተካከሉትም ።

23 ፤ በመንግሥታቸውም ፡ መጨረሻ ፥ ኀጢአታቸው ፡ በተሞላች ፡ ጊዜ ፥ እንቆቅልሽን ፡ የሚያስተውል ፡ ፊተ ፡ ጨካኝ ፡ ንጉሥ ፡ ይነሣል ።

24 ፤ ኀይሉም ፡ ይበረታል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በራሱ ፡ ኀይል ፡ አይደለም ፤ በድንቅም ፡ ያጠፋል ፥ ያደርግማል ፥ ይከናወንማል ፤ ኀያላንንና ፡ የቅዱሳንን ፡ ሕዝብ ፡ ያጠፋል ።

25 ፤ በመታለሉ ፡ ተንኰልን ፡ በእጁ ፡ ያከናውናል ፤ በልቡም ፡ ይታበያል ፥ ታምነውም ፡ የሚኖሩትን ፡ ብዙዎችን ፡ ያጠፋል ፤ በአለቃዎቹም ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ይቋቋማል ፤ ያለ ፡ እጅም ፡ ይሰበራል ።

26 ፤ የተነገረውም ፡ የማታውና ፡ የጧቱ ፡ ራእይ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ስለሚኾን ፡ ራእዩን ፡ ዝጋ ።

27 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ተኘኹ ፥ ዐያሌም ፡ ቀን ፡ ታመምኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቼ ፡ የንጉሡን ፡ ሥራ ፡ እሠራ ፡

270 ዕብ. ፥ ጋብሪኤል ፡ (ገብረ ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ አገልጋይ) ።



www.ethiopianorthodox.org

ነበር ፤ ስለ ፡ ራእዩም ፡ አደንቅ ፡ ነበር ፥ የሚያስተውለው ፡ ግን ፡ አልነበረም ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምዕራፍ ፡ 9 ።

1 ፤ በከለዳውያን ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ በነገሠ ፥ ከሜዶን ፡ ዘር ፡ በነበረ ፡ በአሕሻዊሮስ ፡ ልጅ ፡ በዳርዮስ ፡ በመዠመሪያ ፡
ዓመት ፥

2 ፤ በነገሠ ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ እኔ ፡ ዳንኤል ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መፍረስ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሰባውን ፡
ዓመት ፥ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡ ለነቢዩ ፡ ለኤርምያስ ፡ የተናገረውን ፡ የዓመቱን ፡ ቍጥር ፡ በመጽሐፍ ፡ አስተዋልኹ ።

3 ፤ ማቅ ፡ ለብሼ ፡ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ ስጾም ፡ እጸልይና ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ አምላክ ፡
አቀናኹ ።

4 ፤ ወደ ፡ አምላኬም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለይኹ ፥ ተናዝዤም ፡ እንዲህ ፡ አልኹ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ከሚወዱኽና ፡
ትእዛዝኽን ፡ ከሚፈጽሙ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፡ ታላቅና ፡ የምታስፈራ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥

5 ፤ ኀጢአትን ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፋትንም ፡ አድርገናል ፥ ዐምፀንማል ፥ ከትእዛዝኽና ፡ ከፍርድኽም ፡ ፈቀቅ ፡
ብለናል ፤

6 ፤ በስምኽም ፡ ለነገሥታታችንና ፡ ለአለቃዎቻችን ፡ ለአባቶቻችንም ፡ ለአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የተናገሩትን ፡
ባሪያዎችኽን ፡ ነቢያትን ፡ አልሰማንም ።

7 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጽድቅ ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ለእኛ ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡
ለእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በቅርብና ፡ በሩቅም ፡ ላሉት ፡ አንተን ፡ በበደሉበት ፡ በበደላቸው ፡ ምክንያት ፡ በበተንኽበት ፡ አገር ፡
ኹሉ ፡ የፊት ፡ ዕፍረት ፡ ነው ።

8 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠራን ፡ ለእኛና ፡ ለነገሥታታችን ፡ ለአለቃዎቻችንና ፡ ለአባቶቻችንም ፡
የፊት ፡ ዕፍረት ፡ ነው ።

9 ፤ 10 ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያመፅን ፡ ብንኾን ፥ በባሪያዎቹም ፡ በነቢያት ፡ እጅ ፡ በፊታችን ፡ ባኖረው ፡ በሕጉ ፡
እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባንሰማ ፥ ለጌታ ፡ ለአምላካችን ፡ ምሕረትና ፡
ይቅርታ ፡ ነው ።

11 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ሕግኽን ፡ ተላልፈዋል ፥ ቃልኽንም ፡ እንዳይሰሙ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡
ሠርተናልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ የተጻፈው ፡ መሐላና ፡ ርግማን ፡ ፈሰሰብን ።

12 ፤ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገርንም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በማምጣቱ ፡ በላያችንና ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ በተሾሙት ፡ ፈራጆቻችን ፡ ላይ ፡
የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አጸና ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ከሰማይ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡
አልተደረገም ።

13 ፤ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ መጣብን ፤ ከኀጢአታችንም ፡ እንመለስ ፡
እውነትኽንም ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ወደአምላካችን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አልለመንንም ።

14 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉ ፡ ነገሩን ፡ ጠብቆ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አመጣ ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡
በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ፥ እኛም ፡ ቃሉን ፡ አልሰማንምና ።

15 ፤ አኹንም ፡ ሕዝብኽን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በበረታች ፡ እጅ ፡ ያወጣኽ ፥ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ቀን ፡ ዝና ፡ ለአንተ ፡
ያገኘኽ ፡ ጌታ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ኀጢአትን ፡ ሠርተናል ፥ ክፋትንም ፡ አድርገናል ።

16 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችንና ፡ ስላባቶቻችን ፡ በደል ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ሕዝብኽ ፡ በዙሪያችን ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡
መሰደቢያ ፡ ኾነዋልና ፥ እንደ ፡ ጽድቅኽ ፡ ኹሉ ፡ ቍጣኽና ፡ መዓትኽ ፡ ከከተማኽ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከቅዱስ ፡ ተራራኽ ፡
እንዲመለስ ፡ እለምንኻለኹ ።

17 ፤ አኹንም ፥ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ የባሪያኽን ፡ ጸሎትና ፡ ልመናውን ፡ ስማ ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በፈረሰው ፡ በመቅደስኽ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ስትል ፡ ፊትኽን ፡ አብራ ።

18 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በፊትኽ ፡ የምንለምን ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ምሕረትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ጽድቃችን ፡ አይደለምና ፡
ጆሮኽን ፡ አዘንብለኽ ፡ ስማ ፤ ዐይንኽን ፡ ገልጠኽ ፡ ጥፋታችንና ፡ ስምኽ ፡ የተጠራባትን ፡ ከተማ ፡ ተመልከት ።

19 ፤ አቤቱ ፥ ስማ ፤ አቤቱ ፥ ይቅር ፡ በል ፤ አቤቱ ፥ አድምጥና ፡ አድርግ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስምኽ ፡ በከተማኽና ፡
በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ተጠርቷልና ፥ ስለ ፡ ራስኽ ፡ አትዘግይ ።

20 ፤ እኔም ፡ ገና ፡ ስናገር ፡ ስጸልይ ፥ በኀጢአቴና ፡ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ኀጢአት ፡ ስናዘዝ ፥ በአምላኬም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስለተቀደሰው ፡ ስለአምላኬ ፡ ተራራ ፡ ስለምን ፥

21 ፤ ገናም ፡ በጸሎት ፡ ስናገር ፡ አስቀድሜ ፡ በራእይ ፡ አይቼው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ገብርኤል ፥ እንሆ ፥ እየበረረ ፡
መጣ ፤ በማታም ፡ መሥዋዕት ፡ ጊዜ ፡ ዳሰሰኝ ።

22 ፤ አስተማረኝም ፥ ተናገረኝም ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ጥበብንና ፡ ማስተዋልን ፡ እሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡
አኹን ፡ መጥቻለኹ ።

23 ፤ አንተ ፡ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ነኽና ፥ በልመናኽ ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጥቷል ፥ እኔም ፡ እነግርኽ ፡
ዘንድ ፡ መጥቻለኹ ፤ አኹንም ፡ ነገሩን ፡ መርምር ፥ ራእዩንም ፡ አስተውል ።

24 ፤ ዐመፃን ፡ ይጨርስ ፥ ኀጢአትንም ፡ ይፈጽም ፥ በደልንም ፡ ያስተሰርይ ፥ የዘለዓለምን ፡ ጽድቅ ፡ ያገባ ፥ ራእይንና ፡
ትንቢትን ፡ ያትም ፥ ቅዱስ ፡ ቅዱሳኑንም ፡ ይቀባ ፡ ዘንድ ፡ በሕዝብኽና ፡ በቅድስት ፡ ከተማኽ ፡ ላይ ፡ ሰባ ፡ ሱባዔ ፡
ተቀጥሯል ።

25 ፤ ስለዚህ ፥ ዕወቅ ፡ አስተውልም ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ መጠገንና ፡ መሥራት ፡ ትእዛዙ ፡ ከሚወጣበት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡
አለቃው ፡ እስከ ፡ መሲሕ ፡ ድረስ ፡ ሰባት ፡ ሱባዔና ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ሱባዔ ፡ ይኾናል ፤ ርሷም ፡ በጭንቀት ፡ ዘመን ፡
ከጕዳናና ፡ ከቅጥር ፡ ጋራ ፡ ትሠራለች ።

26 ፤ ከስድሳ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሰባትም ፡ በኋላ ፡ መሲሕ ፡ ይገደላል ፥ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለም ፤ የሚመጣውም ፡
አለቃ ፡ ሕዝብ ፡ ከተማዪቱንና ፡ መቅደሱን ፡ ያጠፋሉ ፤ ፍጻሜውም ፡ በጐርፍ ፡ ይኾናል ፥ እስከ ፡ መጨረሻም ፡ ድረስ ፡
ጦርነት ፡ ይኾናል ፤ ጥፋትም ፡ ተቀጥሯል ።

27 ፤ ርሱም ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ጽኑ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላንድ ፡ ሱባዔ ፡ ያደርጋል ፤ በሱባዔውም ፡ እኩሌታ ፡
መሥዋዕቱንና ፡ ቍርባኑን ፡ ያስቀራል ፤ በርኵሰትም ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አጥፊው ፡ ይመጣል ፤ እስከተቈረጠውም ፡ ፍጻሜ ፡
ድረስ ፡ መቅሠፍት ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምዕራፍ ፡ 10 ።

1 ፤ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ብልጣሶር ፡ ለተባለው ፡ ለዳንኤል ፡ ነገር ፡ ተገለጠለት ፤ ነገሩም ፡
እውነት ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ነው ፤ ነገሩንም ፡ አስተዋለ ፥ በራእዩም ፡ ውስጥ ፡ ማስተዋል ፡ ተሰጠው ።

2 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እኔ ፡ ዳንኤል ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ሳዝን ፡ ነበር ።

3 ፤ ማለፊያ ፡ እንጀራም ፡ አልበላኹም ፥ ሥጋና ፡ ጠጅም ፡ በአፌ ፡ አልገባም ፥ ሦስቱም ፡ ሳምንት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡
ዘይት ፡ አልተቀባኹም ።

4 ፤ ከመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ጤግሮስ ፡ በተባለው ፡ በታላቁ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡
ሳለኹ ፥ ዐይኔን ፡ አነሣኹ ፥

5 ፤ እንሆም ፥ በፍታ ፡ የለበሰውን ፡ ጥሩም ፡ የአፌዝን ፡ ወርቅ ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ የታጠቀውን ፡ ሰው ፡ አየኹ ።

6 ፤ አካሉም ፡ እንደ ፡ ቢረሌ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፥ ፊቱም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ምስያ ፡ ነበረ ፥ ዐይኖቹም ፡ እንደሚንበለበል ፡
ፋና ፥ ክንዶቹና ፡ እግሮቹም ፡ እንደ ፡ ጋለ ፡ ናስ ፥ የቃሉም ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ ነበረ ።

7 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ብቻዬን ፡ ራእዩን ፡ አየኹ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ራእዩን ፡ አላዩም ፤ ነገር ፡



www.ethiopianorthodox.org

ግን ፥ ጽኑ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ወደቀባቸው ፥ ሊሸሸጉም ፡ ሸሹ ።

8 ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ቀረኹ ፡ ይህንም ፡ ታላቅ ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ ኀይልም ፡ አልቀረልኝም ፥ ደም ፡ ግባቴም ፡ ወደ ፡ ማሸብሸብ ፡ ተለወጠብኝ ፥ ኀይልም ፡ ዐጣኹ ።

9 ፤ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፤ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ።

10 ፤ እንሆም ፥ አንዲት ፡ እጅ ፡ ዳሰሰችኝ ፥ በጕልበቴና ፡ በእጄም ፡ አቆመችኝ ።

11 ፤ ርሱም ፦ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ሰው ፡ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወዳንተ ፡ ተልኬያለኹና ፡ የምነግርኽን ፡ ቃል ፡ አስተውል ፥ ቀጥ ፡ ብለኽም ፡ ቁም ፡ አለኝ ። ይህንም ፡ ቃል ፡ ባለኝ ፡ ጊዜ ፡ እየተንቀጠቀጥኹ ፡ ቆምኹ ።

12 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ ልብኽ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፥ ሰውነትኽም ፡ በአምላክኽ ፡ ፊት ፡ ይዋረድ ፡ ዘንድ ፡ ካደረግኽበት ፡ ከመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ቃልኽ ፡ ተሰምቷል ፤ እኔም ፡ ስለ ፡ ቃልኽ ፡ መጥቻለኹ ።

13 ፤ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተቋቋመኝ ፤ እንሆም ፥ ከዋነኛዎቹ ፡ አለቃዎች ፡ አንዱ ፡ ሚካኤል ፡ ሊረዳኝ ፡ መጣ ፤ እኔም ፡ ከፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ተውኹት ።

14 ፤ ራእዩም ፡ ገና ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ነውና ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ለሕዝብኽ ፡ የሚኾነውን ፡ አስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፡ አኹን ፡ መጥቻለኹ ።

15 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ በተናገረኝ ፡ ጊዜ ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አቀረቀርኹ ፥ ዲዳም ፡ ኾንኹ ።

16 ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ከንፈሬን ፡ ዳሰሰኝ ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አፌን ፡ ከፍቼ ፡ ተናገርኹ ፡ በፊቴም ፡ ቆሞ ፡ የነበረውን ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ከራእዩ ፡ የተነሣ ፡ ሕመሜ ፡ መጣብኝ ፥ ኀይልም ፡ ዐጣኹ ።

17 ፤ ይህ ፡ የጌታዬ ፡ ባሪያ ፡ ከዚህ ፡ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፡፡ አኹንም ፡ ኀይል ፡ ዐጣኹ ፥ እስትንፋስም ፡ አልቀረልኝም ፡ አልኹት ።

18 ፤ ደግሞ ፡ ሰው ፡ የሚመስል ፡ ዳሰሰኝ ፥ አበረታኝም ።

19 ፤ ርሱም ፦ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፤ በርታ ፥ ጽና ፡ አለኝ ። በተናገረኝም ፡ ጊዜ ፡ በረታኹና ፦ አበርትተኸኛልና ፥ ጌታዬ ፡ ይናገር ፡ አልኹ ።

20 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ወዳንተ ፡ የመጣኹት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ታውቃለኽን ፡፡ አኹንም ፡ ከፋርስ ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ እዋጋ ፡ ዘንድ ፡ እመለሳለኹ ፤ እኔም ፡ ስወጣ ፥ እንሆ ፤ የግሪክ ፡ አለቃ ፡ ይመጣል ።

21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእውነት ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈውን ፡ እነግርኻለኹ ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ከአለቃችኹ ፡ ከሚካኤል ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የሚያጸናኝ ፡ የለም ።

## __________________ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 11 ።

1 ፤ እኔም ፡ በሜዶናዊ ፡ በዳርዮስ ፡ መዠመሪያ ፡ ዓመት ፡ አጸናውና ፡ አበረታው ፡ ዘንድ ፡ ቆሜ ፡ ነበር ።

2 ፤ አኹንም ፡ እውነትን ፡ አሳይኻለኹ ። እንሆ ፥ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ ደግሞ ፡ በፋርስ ፡ ይነሣሉ ፤ አራተኛውም ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ይኾናል ፤ በባለጠግነቱም ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ በግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ኹሉን ፡ ያስነሣል ።

3 ፤ ኀያልም ፡ ንጉሥ ፡ ይነሣል ፥ በትልቅ ፡ አገዛዝም ፡ ይገዛል ፥ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ ያደርጋል ።

4 ፤ ርሱም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ ይሰበራል ፤ እስከ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ ይከፋፈላል ። ለዘሩ ፡ ግን ፡ አይከፋፈልም ፥ እንደ ፡ ገዛበትም ፡ አገዛዝ ፡ አይኾንም ፤ መንግሥቱ ፡ ይነቀላልና ፤ ከነዚህም ፡ ለሌላዎች ፡ ይኾናልና ።

5 ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ከአለቃዎቹም ፡ አንዱ ፡ ይበረታሉ ፤ ርሱም ፡ ይበረታበታል ፡ ይሠለጥንማል ፤ ግዛቱም ፡ ታላቅ ፡ ግዛት ፡ ይኾናል ።

6 ፤ ከዘመናትም ፡ በኋላ ፡ ይጋጠማሉ ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማድረግ ፡ ወደሰሜን ፡ ንጉሥ ፡



www.ethiopianorthodox.org

ትመጣለች ፤ የክንዷ ፡ ኀይል ፡ ግን ፡ አይጸናም ፥ ርሱና ፡ ክንዱም ፡ አይጸናም ፤ ርሷና ፡ ርሷን ፡ ያመጡ ፡ የወለዳትም ፡
በዚያም ፡ ዘመን ፡ ያጸናት ፡ ዐልፈው ፡ ይሰጣሉ ።

7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሥሯ ፡ ቊጥቋጥ ፡ አንዱ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ወደ ፡ ሰራዊቱም ፡ ይመጣል ፥ ወደሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡
ዐምባ ፡ ይገባል ፥ በላያቸውም ፡ ያደርጋል ፥ ያሸንፍማል ።

8 ፤ አማልክታቸውንና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ከብርና ፡ ከወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ የከበሩትን ፡
ዕቃዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይማርካል ፤ እስከ ፡ ጥቂትም ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ሳይዋጋ ፡ ይቀመጣል ።

9 ፤ ይህም ፡ ወደደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ መንግሥት ፡ ይገባል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደገዛ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ።

10 ፤ ልጆቹም ፡ ይዋጋሉ ፤ ብዙ ፡ ሰራዊትንና ፡ ሕዝብን ፡ ይሰበስባል ፤ ርሱም ፡
ይመጣል ፥ ይጐርፍማል ፥ ያልፍማል ፤ ተመልሰም ፡ እስከ ፡ ዐምባው ፡ ድረስ ፡ ይዋጋል ።

11 ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ይቈጣል ፡ ወጥቶም ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ፤ ብዙ ፡ ሕዝብንም ፡ ለሰልፍ ፡
ያቆማል ፥ ሕዝቡም ፡ ዐልፎ ፡ በእጁ ፡ ይሰጣል ።

12 ፤ ሕዝቡም ፡ በተወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ይታበያል ፤ አእላፋትንም ፡ ይጥላል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አያሸንፍም ።

13 ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመለሳል ፥ ከቀደመውም ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ለሰልፍ ፡ ያቆማል ፤ በዘመናትና ፡
በዓመታትም ፡ ፍጻሜ ፡ ከታላቅ ፡ ሰራዊትና ፡ ከብዙ ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ።

14 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፤ ከሕዝብኽም ፡ መካከል ፡ የዐመፅ ፡ ልጆች ፡
ራእዩን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ይነሣሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይወድቃሉ ።

15 ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል ፥ ዐፈርንም ፡ ይደለድላል ፥ የተመሸገችንም ፡ ከተማ ፡ ይወስዳል ፤ የደቡብም ፡
ሰራዊት ፡ የተመረጡትም ፡ ሕዝቡ ፡ አይቆሙም ፤ ለመቋቋምም ፡ ኀይል ፡ የላቸውም ።

16 ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ የሚመጣው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፥ በፊቱም ፡ የሚቆም ፡ የለም ፤ በመልካሚቱም ፡
ምድር ፡ ይቆማል ፥ በእጁም ፡ ውስጥ ፡ ጥፋት ፡ ይኾናል ።

17 ፤ ከመንግሥቱም ፡ ኹሉ ፡ ኀይል ፡ ጋራ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ፊቱን ፡ ያቀናል ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድነትን ፡
ያደርጋል ፤ ያረክሳትም ፡ ዘንድ ፡ ሴትን ፡ ልጅ ፡ ይሰጠዋል ፤ ርሷም ፡ አትጸናም ፡ ለርሱም ፡ አትኾንም ።

18 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ደሴቶች ፡ ይመልሳል ፥ ብዙዎችንም ፡ ይወስዳል ፤ አንድ ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ስድቡን ፡
ይሽራል ፥ ስድቡንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ።

19 ፤ ፊቱንም ፡ ወደገዛ ፡ ምድሩ ፡ ዐምባዎች ፡ ይመልሳል ፤ ተሰናክሎም ፡ ይወድቃል ፥ አይገኝምም ።

20 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በመንግሥቱ ፡ ክብር ፡ መካከል ፡ አስገባሪውን ፡ የሚያሳልፍ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ነገር ፡
ግን ፥ በቍጣው ፡ ሳይኾን ፡ በሰልፍም ፡ ሳይኾን ፡ በጥቂት ፡ ቀን ፡ ይሰበራል ።

21 ፤ በርሱም ፡ ስፍራ ፡ የተጠቃ ፡ ሰው ፡ ይነሣል ፡ የመንግሥቱንም ፡ ክብር ፡ አይሰጡትም ፤ በቀስታ ፡ መጥቶ ፡
መንግሥቱን ፡ በማታለል ፡ ይገዛል ።

22 ፤ የሚጐርፍም ፡ ሰራዊት ፡ ከፊቱ ፡ ይወሰዳል ፥ ርሱና ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ አለቃ ፡ ይሰበራሉ ።

23 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከተወዳጀ ፡ በኋላ ፥ በተንኰል ፡ ያደርጋል ፤ ከጥቂትም ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ወጥቶ ፡ ይበረታል ።

24 ፤ በቀስታ ፡ ከአገር ፡ ኹሉ ፡ ወደለመለመችው ፡ ክፍል ፡ ይገባል ፤ አባቶቹና ፡ የአባቶቹ ፡ አባቶች ፡ ያላደረጉትንም ፡
ያደርጋል ፤ ብዝበዛውንና ፡ ምርኮውንም ፣ ሀብቱንም ፡ በመካከላቸው ፡ ይበትናል ፤ በምሽጎችም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡
ድረስ ፡ ዐሳቡን ፡ ይፈጥራል ።

25 ፤ በታላቅም ፡ ሰራዊት ፡ ኾኖ ፡ ኀይሉንና ፡ ልቡን ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ያስነሣል ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ በታላቅና ፡
በብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ኾኖ ፡ በሰልፍ ፡ ይዋጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐሳብ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይፈጥራሉና ፥ አይጸናም ።

26 ፤ መብሉንም ፡ የሚበሉ ፡ ሰዎች ፡ ይሰብሩታል ፤ ሰራዊቱም ፡ ይጐርፋል ፤ ብዙዎችም ፡ ተገድለው ፡ ይወድቃሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

27 ፤ እነዚህም ፡ ኹለት ፡ ነገሥታት ፡ ክፋትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በልባቸው ፡ ያስባሉ ፥ ባንድ ፡ ገበታም ፡ ተቀምጠው ፡
ሐሰት ፡ ይናገራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፍጻሜው ፡ እስከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፥ አይከናወንላቸውም ።

28 ፤ ከብዙም ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ፥ ልቡም ፡ በተቀደሰ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡
ይኾናል ፤ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ፥ ወደገዛ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ።

29 ፤ በተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ ይመለሳል ፥ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ይመጣል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኋለኛው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡
አይኾንም ።

30 ፤ የኪቲም ፡ መርከቦች ፡ ይመጡበታልና ፥ ስለዚህ ፡ ዐዝኖ ፡ ይመለሳል ፥ በቅዱሱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡
ይቈጣል ፥ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ፤ ተመልሶም ፡ ቅዱሱን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የተዉትን ፡ ሰዎች ፡ ይመለከታል ።

31 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሰራዊቶች ፡ ይቆማሉ ፥ መቅደሱንም ፣ ግንቡንም ፡ ያረክሳሉ ፥ የዘወትሩንም ፡ መሥዋዕት ፡
ያስቀራሉ ፥ የጥፋትንም ፡ ርኵሰት ፡ ያቆማሉ ።

32 ፤ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ የሚበድሉትንም ፡ በማታለል ፡ ያስታል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካቸውን ፡ የሚያውቁ ፡ ሕዝብ ፡
ይበረታሉ ፥ ያደርጋሉም ።

33 ፤ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ጥበበኞዎች ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያስተምራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰይፍና ፡ በእሳት ፡
ነበልባል ፡ በምርኮና ፡ በመበዝበዝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይወድቃሉ ።

34 ፤ በወደቁም ፡ ጊዜ ፡ በጥቂት ፡ ርዳታ ፡ ይረዳሉ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በግብዝነት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተባብረው ፡
ይሰበሰባሉ ።

35 ፤ እስከተወሰነውም ፡ ዘመን ፡ ይኾናልና ፥ ከጥበበኞዎቹ ፡ ዐያሌዎቹ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ይነጥሩና ፡
ይጠሩ ፣ ይነጡም ፡ ዘንድ ፡ ይወድቃሉ ።

36 ፤ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፤ ራሱንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ በአማልክት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡
ታላቅ ፡ ያደርጋል ፥ በአማልክትም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ በትዕቢት ፡ ይናገራል ፤ ቍጣም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡
ይከናወንለታል ፥ የተወሰነው ፡ ይደረጋልና ።

37 ፤ የአባቶቹንም ፡ አማልክት ፡ የሴቶችንም ፡ ምኞት ፡ አይመለከትም ፤ ራሱንም ፡ በኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡
ያደርጋልና ፥ አማልክትን ፡ ኹሉ ፡ አይመለከትም ።

38 ፤ በእነዚህ ፡ ፋንታ ፡ ግን ፡ የዐምባዎቹን ፡ አምላክ ፡ ያከብራል ፤ አባቶቹም ፡ ያላወቁትን ፡ አምላክ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡
በዕንቍና ፡ በከበረ ፡ ነገር ፡ ያከብረዋል ።

39 ፤ በእንግዳም ፡ አምላክ ፡ ርዳታ ፡ በጽኑ ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፤ ለሚያውቁት ፡ ክብር ፡ ያበዛላቸዋል ፥ በብዙም ፡
ላይ ፡ ያስገዛቸዋል ፥ ምድርንም ፡ በዋጋ ፡ ይከፍላል ።

40 ፤ በፍጻሜ ፡ ዘመንም ፡ የደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ከሠረገላዎችና ፡
ከፈረሰኞዎች ፡ ከብዙም ፡ መርከቦች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣበታል ፤ ወደ ፡ አገሮችም ፡
ይገባል ፥ ይጐርፍማል ፥ ያልፍማል ።

41 ፤ ወደ ፡ መልካሚቱም ፡ ምድር ፡ ይገባል ፥ ብዙ ፡ አገሮችም ፡ ይወድቃሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኤዶምያስና ፡ ሞዐብ ፡
ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ የበለጡት ፡ ከእጁ ፡ ይድናሉ ።

42 ፤ እጁን ፡ በአገሮች ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥ የግብጽም ፡ ምድር ፡ አታመልጥም ።

43 ፤ በወርቅና ፡ በብርም ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፥ በከበረችም ፡ በግብጽ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥናል ፤ የልብያና ፡
የኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ይከተሉታል ።

44 ፤ ከምሥራቅና ፡ ከሰሜን ፡ ግን ፡ ወሬ ፡ ያውከዋል ፤ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ይገድል ፡ ዘንድና ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡
በታላቅ ፡ ቍጣ ፡ ይወጣል ።

45 ፤ ንጉሣዊ ፡ ድንኳኑንም ፡ በባሕርና ፡ በከበረው ፡ በቅዱስ ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ ይተክላል ፤ ወደ ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡



www.ethiopianorthodox.org

ይመጣል ፥ ማንም ፡ አይረዳውም ።

## ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ምዕራፍ ፡ 12 ።

1 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ስለሕዝብኽ ፡ ልጆች ፡ የሚቆመው ፡ ታላቁ ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል ፡ ይነሣል ፤ ሕዝብም ፡ ከኾነ ፡
ዠምሮ ፡ እስከዚያ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ያልኾነ ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ ይኾናል ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡
በመጽሐፉ ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘው ፡ ሕዝብኽ ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ይድናል ።

2 ፤ በምድርም ፡ ትቢያ ፡ ውስጥ ፡ ካንቀላፉቱ ፡ ብዙዎች ፡ ይነቃሉ ፤ እኩሌቶቹ ፡ ወደዘለዓለም ፡ ሕይወት ፥ እኩሌቶቹም ፡
ወደ ፡ ዕፍረትና ፡ ወደዘለዓለም ፡ ጕስቍልና ።

3 ፤ ጥበበኛዎቹም ፡ እንደሰማይ ፡ ጸዳል ፥ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚመልሱ ፡ እንደ ፡ ከዋክብት ፡ ለዘለዓለም ፡
ይደምቃሉ ።

4 ፤ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ቃሉን ፡ ዝጋ ፥ መጽሐፉንም ፡ ዐትም ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡
ይመረምራሉ ፥ ዕውቀትም ፡ ይበዛል ።

5 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ሌላዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ አንዱ ፡ በዚህ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፥ ሌላውም ፡
በዚያ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ።

6 ፤ አንዱም ፡ ከወንዙ ፡ ውሃ ፡ በላይ ፡ የነበረውን ፡ በፍታም ፡ የለበሰውን ፦ የዚህ ፡ ድንቅ ፡ ፍጻሜ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡
ነው ፧ አለው ።

7 ፤ ከወንዙም ፡ ውሃ ፡ በላይ ፡ የነበረው ፡ በፍታም ፡ የለበሰው ፡ ሰው ፡ ቀኙና ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡
አንሥቶ ፦ ለዘመንና ፡ ለዘመናት ፡ ለዘመንም ፡ እኩሌታ ፡ ነው ፤ የተቀደሰውም ፡ ሕዝብ ፡ ኀይል ፡ መበተን ፡ በተጨረሰ ፡
ጊዜ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸማል ፡ ብሎ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ በሚኖረው ፡ሲምል ፡ ሰማኹ ።

8 ፤ ሰማኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላስተዋልኹም ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ የዚህ ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ አልኹ ።

9 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ቃሉ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተዘጋና ፡ የታተመ ፡
ነውና ፥ ኺድ ፤

10 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያጠራሉ ፥ ያነጡማል ፥ ይነጥሩማል ፤ ክፉዎች ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡
ያደርጋሉ ፤ ክፉዎችም ፡ ኹሉ ፡ አያስተውሉም ፥ ጥበበኛዎች ፡ ግን ፡ ያስተውላሉ ።

11 ፤ የዘወትሩም ፡ መሥዋዕት ፡ ከቀረ ፡ ዠምሮ ፥ የጥፋትም ፡ ርኵሰት ፡ ከቆመ ፡ ዠምሮ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡
ቀን ፡ ይኾናል ።

12 ፤ የሚታገሥ ፥ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ቀንም ፡ የሚደርስ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

13 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ድረስ ፡ ኺድ ፤ አንተም ፡ ታርፋለኽ ፥ በቀኑም ፡ መጨረሻ ፡ በዕጣ ፡ ክፍልኽ ፡
ትቆማለኽ ❖



www.ethiopianorthodox.org